# ዐራት ትፍጽምት ያለው ግጥም

## ፭ኛ

ድብር ባለበት ቀን ጭጋግ በለበሰ
ያ ክፉ ጅብ መጣ እያነካከሰ
አህያየ ጠፍታ ስፈልጋት ውየ
ደክሞኝ ቤቴ ገባሁ ጠፍታ ትቅር ብየ
አሁን በጨለማ ከምንከራተት
ግድ የለም ያ ሽባ እንዳሻው ያ'ርጋት
በማለት በእርጋታ ካልጋየ ገበቼ
ለጥ ብየ አደርኩኝ በሰላም ተኝቼ።

ጥዋት ተነስቼ ወደ ውጩ ሳይ
ከቤቴ በወድያ ከቅብቅቡ ላይ
ያችው አህያየ ሳሯን እየጋጠች
"የጠፋሁ መስሎት ነው?" ብላ እየሳቀች
ገልመጥ ብላ አይታኝ መጋጥዋን ቀጠለች።

ተመስገን አምላኬ እንኳን ያልኮነንከኝ
ምስጋና ይድረስህ ከድካም ያዳንከኝ
አህያየ አልጠፋች እኔ አልተንከራተትኩ
ከሞቀው አልጋየ ተኝቼ ስላደርኩ

ገ/ኢ. ጐርፉ።

ይቀጥላል…

# ዐራት ትፍጽምት ያለው ግጥም

፪

ደብር ባለበት ቀን ጭጋግ በለበሰ
ያ ክፉ ጅብ መጣ እያነካከሰ
አህያየ ጠፍታ ስፈልጋት ውየ
ደክሞኝ ቤቴ ገባሁ ጠፍታ ትቅር ብየ
በሰላም፣ በእርጋታ እራቴን በልቼ
ትራስ ተንተርሼ፣ ጠላየን ጠጥቼ
ለጥ ብየ ተኛሁ ከአልጋየ ገብቼ
ታድያ እኩለ ሌሊት ጅብ ሲጮህ ሰምቼ
ትንሽ ተገላበጥኩ ከእንቅልፌ ነቅቼ
ግን ጉድ ነው ያየሁት ጥዋት ተነስቼ…
 ከቤቴ በወድያ ከቅብቅቡ ላይ
 ምስኪኒቱ ፍጡር ጉድ ሆነሻል ወይ!
 አወይ አህያየ ግንጥልጥሏ ወጥቶ
 እግሯ፣ ሽኾናዋ ወዲያ ተዘርግቶ
 አንጀት፣ ሆድ ዕቃዋ ፍጹም ተበትብቶ
 ጠቅላላው ስጋዋ በጅቡ ተበልቶ
 ብጥስጥሷ ወጥቶ፣ ዓጽሟ ብቻ ቀርቶ
 ብትንትን ብላለች ሜዳው ሁሉ ሞልቶ።
ምነው ባልሰንፍ ኖሮ ትላንትና ማታ
ጅቡን እንዳየሁት መላ-ምት ብመታ
ተከትየው ዞሬ ትንሽ ብንገላታ
ቁልቁለት ወርጄ፣ ብወጣ ኮረብታ
ምን አጉል ቀን ዋልኩኝ የፈጠርከኝ ጌታ!
አድናት ነበረ እንዲህ ካለው ሞት
ግን ፈጣሪ ፈርዶ ይብቃሽ ስላላት
ቀኗ ደረሰና ያው አለቀላት፣
ጅቡም እንዳይርበው ሆነችው እራት፣
እኔም ብየ ነበር እንዳሻው ያ'ርጋት
ለዚህ ነው መሰለኝ ያነካከታት
አላምጦ፣ አኝኮ፣ ውጦ፣ የበላት።
 ቀኗ ከደረሰ መቸም ላላድናት
 ብደክም ባልደክም ሞት ለማይቀርላት
 እንኳን አልደከምኹኝ፣ አልተንከራተትኩኝ
 ከሞቀ አልጋየ ውስጥ ተኝቼው ያደርኩኝ።

ገ/ኢ. ጐርፉ።

ይቀጥላል…

## ዐራት ትፍጽምት ያለው ግጥም
## ፫

ደብር ባለበት ቀን ጭጋግ በለበሰ
ያ ክፉ ጅብ መጣ እያነካከሰ፣
አህያየ ጠፍታ ስፈልጋት ውየ
ቤት ልመለስ ነበር ጠፍታ ትቅር ብየ
“ግን ያ ክፉ ሽባ ያገኛት እንደሆን
ጸጸቱ አይወጣልኝ መቸውኑም ቢሆን…”
እያልኩ ተከትየው ዱር ለዱር ስጓዝ
ሜዳና፣ ተራራ፣ ሸለቆና፣ ወንዝ፣
ወጣሁኝ፣ ወረድኹኝ፣ ያንን ሁሉ በእግሬ
ሌ’ቱም ጨለመና ስኳትን አድሬ
ጥዋት ቤት ስገባ በድካም ሰክሬ
ከቶ ማን ሰው ይሆን የቆመው ከበሬ?
ኦረ ሰው አይደለም፣ ሰውስ የመሰለኝ
ለካ አህያየ ናት፣ ምንኛ ደስ አለኝ!
ከምንም ሳልቆጥረው ጨለማ ሌሊቱ
ዕንቅፋት ሲመታኝ፣ መውደቅ፣ መነሳቱ
ቁልቁለት ወርጄ፣ ስወጣ ዳገቱ፣
ወድያውኑ ረሳሁት ድካሙ፣ ልፋቱ።
ጠፋ ያሉት ንብረት እንዲህ መገኘቱ
መግለጽ ያዳግታል፣ አወይ ደስ ማለቱ!
ገ/ኢ. ጕርፉ።

ይቀጥላል…

# ዐራት ትፍጽምት ያለው ግጥም
# ፬



ድብር ባለበት ቀን ጭጋግ በለበሰ
ያ ክፉ ጅብ መጣ እያነካከሰ
አህያየ ጠፍታ ስፈልጋት ውየ
ቤት ልመለስ ነበር ጠፍታ ትቅር ብየ
‘ግን ያ ክፉ ሽባ ያገኛት እንደሆን
ጸጸቱ አይወጣልኝ መቸውኑም ቢሆን…’
ብየ ተከትየው ዱር-ለዱር ስንዝ
ሜዳና፣ ተራራ፣ ሸለቆና፣ ወንዝ፣
ወጣሁኝ፣ ወረድኹኝ፣ ያንን ሁሉ በ’ግሬ
ሌ’ቱም ጨለመና ስኳትን አድሬ
ጥዋት ቤት ስገባ በድካም ሰክሬ
ያች ሓፍረተ-ቢሷ ቆማለች ከበሬ!
“ወየት አባሽ አደርሽ?” ብየ ተናድጄ
ዠለጥኳት በያዝኩት ዱላ በቀኝ እጄ
“ኦረ አንተው የት አደርክ?” ብላ ተገልብጣ
አሽቀነጠረችኝ ወደ ኋላ ረግጣ።
“ኦረ! እንዲህ ናትና…” ብየ ተነስቼ
ድብን ላ’ረጋት ስል ሽጉጤን አውጥቼ፣
“ተው እኮ ምን ነካህ፣ ጤናም አይደለህ?
ጅብዱ ሊባል ነው ወይ አህያህ ገድለህ?”
ብላ በመገረም ዓይኖቿን አፍጥጣ
ትጠይቀኝ ጀመር ደፋር፣ ዓይን አውጣ፤
“እስኪ ምን በደልኩህ በዚህ በማለዳ
“የምታወርድብኝ የዱላህን ናዳ?
“ቤቱን ዘግተህ ሄደህ፣ መግቢያም አጥቼ
“ስጠብቅ አድሬ፣ ከውጭ ተኀልቼ
“የትም ስትሰክር፣ ስትዞር አድረህ
“ኦረ ለመሆኑ ምን ዓይነት ሰው ነህ?
“ምንም ሳትጠይቅ ጉዳይ አስለህ
“እንዲያው መማታቱ ማለዳ መጥተህ
“እንዲህ ያለ በደል ሰውም አይስማህ።
“ኀረቤት ይፍረደው ዘመድ ይሁን ባዳ
“ምክንያትም ካለህ ዘርዝርና አስረዳ…”



“ዝም በዬ ለፍላፊቱ፣ ሰማሁልሽ በቃ
“ልደባልቅሽ ነው ካፈርና ጭቃ
“አንድም ቃል አይውጣሽ፣ አፍሽንም ዝጊው
“ፈጣሪን ከልብሽ ይቅርታ ጠይቂው።
“ጌታሽን በእርግጫ ከሆዴ መትተሽ
“ደግሞ መሞጣሞጥ፣ ፍጹም አልለቅሽ!
“እኔ ቆርጫለሁ፣ አልቆልሻልና
“ቶሎ ተዘጋጂ ንስሓ ግቢና...”
ብየ አቀባበልኩት፣ ሽጉጡም ጎረሰ
የመሞቻዋ ቀን ዕለቱ ደረሰ
ወስጄ ደገንኩት ከግንባሯ ላይ
አይገድለኝም ብላ ዓይን-ዓይኔን ስታይ
የመሞቻዋ ቀን በእርግጥ ደረሰ
ቃታውን ስስበው ግንባሯ ፈረሰ
ጥይቱ ገባና ወደ አንጎሏ ውስጥ
አጨማለቀልኝ አ'ርጎ ፍርጥርጥ።
ወድቃ፣ ተንፈራፍራ፣ ከእግሮቼ በታች
በቃት አህያየ ወድያውኑ ሞተች።



እስቲ ምን ይባላል እኔው ከምገድላት
ከዚያው ከዱር ጠፍታ ያ ጅብስ በበላት!
ዓርፌ፣ ተኝቼ ከአልጋየ ባደርኩኝ
ተራራ፣ ሸለቆ፣ ባልተንከራተትኩኝ!
ምንኛ ዕድለኛ፣ ጤና ሰው በሆንኩኝ!
ሌቱን ሙሉ ስዞር ድካሜ እንዲያ በዝቶ
እግሬ፣ አውራ ጣቴ ዕንቅፋት ተመትቶ
ማለዳም በእርግጫ ሆዴ ተነርቶ
በዚያች በገጣባ፣ ጀርባዋ ድሪቶ
ምላሷ ሾለብኝ ወጣ ተዘርግቶ
በእርሷስ የተነሳ አልታደልኩም ከቶ!
አሁን ከበራፌ ጥንቧ ተጎልቶ
ቶሎ ካልተጣለ ጫካ ተጎትቶ
ጉዴ ሊፈላ ነው ሰፈር ሁሉ ገምቶ...
ይህ የመሰለ ጉድ እስኪ ከየት መጣ?
አያድርስባችሁ እንዲህ ያለ ጣጣ
መዓት ነው ዘንድሮ፣ ኦረ ጉዴ ወጣ!



ገ/ኢ. ጐርፉ።

***Back to Meskot***

---

***The views reflected in the above poem/article are solely of the author and are not necessarily shared by*** *Meskot* ***. You may contact G.E. Gorfu for comments at*** gegorfu@yahoo.com.